# ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ ለአብ ሁሉን የሠራ በጥበብ

ሃሌ ሉያ ለወልድ ሰውን እስከ ሞት የሚወድ

ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ፍጥረቱን ሁሉ የሚቀድስ

አዝ . . . . .

ይገባዋልና ክብርና ውዳሴ

አንድ አምላክ ለሚሆን ለቅድስት ሥላሴ

ዘወትር እናመስግን ስሙን በቅዳሴ

የአሮንን አምላክ እንዲሁም የሙሴ

አዝ . . . . ..

መላእክቱ ሁሉ ያመሰገኑት

ቅዱሳኑም ሁሉ የተገዙለት

ግሩም ነው ድንቅ ነው ኃያል መለኮት

ዘላለም ክብር ይግባው ፍጹም በእውነት

አዝ . . . . .

ዘላለም የጸና የሚገባው ክብር

አንዳች ነገር የለም ከቶ የሚሳነው

የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ድንቅ ነው